# ለመለስ ዜናዊ ያልተነፈገውን ለብርሃኑ ነጋ ይሰጠዋል

**የነጻነት ጎህ ሲቀድ፡ ሊቀለበስ የተሞከረው የኢትዮጵያ ዴሞክራሲ**
**ብርሃኑ ነጋ**

**አቃቂር፡ ገላወዴዎስ ኣርኣያ**

ይህ አቃቂር በመሰረቱ ከሌሎቹ ጽሑፎቼ በይዘትና በአጠቃላይ የትንታኔ ስልቱ አይለይም። በተቻለ መጠን ፍትሓዊ፡ ትምህርታዊና ገለልተኛ ጸሑፍ (ሂስ ያካተተ ቢሆንም) ላንባብያን ከቀረበ፡ በርትዓዊነቱ ብቻ ሳይሆን ባቀራረብ ዘይቤና በስነጽሑፍ አያልነቱ (power of literary criticism) የሕብረተሰብ አባላትን ይጠቅማል፡ ትምህርታዊና ሰላማዊ መንገድ ይቀይሳል፡ የወጣት ትውልድም አእምሮ አወንታዊ በሆነ መንገድ ያንጻል የሚል እምነት አለኝ። አንዱ የትምህርት ዓላማም ይኸው ነው። ስለሆነም ከዚሁ መንፈስ በመነሳት ከዚህ ቀደም ለጠቅላይ ሚኒስተር መለስ ዜናዊ ያልተነፈገውን ("Reflections on 'African Development: Dead Ends and New Beginnings,'" [www.africanidea.org/reflections_mz.html](www.africanidea.org/reflections_mz.html) ተመልከት) አሁን ለ ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ ይሰጠዋል።

ከፍ ብየ እንደጠቀስኩት ይህ አቃቂር ፍትሓዊና ርትዓዊ መሆን ስላለበት በብርሃኑ መጽሓፍ (*የነጻነት ጎህ ሲቀድ*) ውስጥ የቀረቡትን አጠቃላይ ትንታኔዎች፡ ጽንሰ ሓሳቦችና ሂሶች የምስማማባቸውና የማልስማማባቸው ነጥቦች በግልጽ አቅርቤዋቸዋለሁ። አንባቢው ታድያ በትዕግስትና በጽሞና ከኔ ጋር ለተወሰነ ግዜ እንዲጓዝ በትህትና እጠይቃለሁ።

መጽሓፉ በአጠቃላይ ይዘቱና አቀራረቡ በቅርቡ በኢትዮጵያ ውስጥ ከተጻፉ መጻሕፍት አንጻር ሲታይ በጣም ጠንካራና የሚደነቅም ነው ማለት ይቻላል። ነገር ግን አንዳንድ ግድፈት ሊኖረው ስለሚችል በሚቀጥሉት ገጾች ለማሳየት እሞክራለሁ። 'አንድን መጽሓፍ በጥራዝነቱ አትፍረደው' የሚለውን መርህ በመከተል ይኸንን መጽሓፍ በተመለከተ እያንዳንዱ መስመርና ገጽ በጥሞና ለማንበብ ተገድጀያለሁ። Alice in the Wonderland በሚለው መጽሓፍ ውስጥ ታሪክ ተናጋሪው ንጉሱን "ጃንሆይ ከየት ልጀምር" ብሎ ጠየቃቸውና ንጉሱም "ከመጀመርያው ጀምር" ብለው መለሱለት ይባላል። እኔም ከመጀመርያው ልጀምርና፡ የመጽሓፉን አርእስት በተመለከተ በመጠኑም ቢሆን ላትት። የመጽሓፉ አርእስት *የነጻነት ጎህ ሲቀድ፡ ሊቀለበስ የተሞከረው የኢትዮጵያ ዴሞክራሲ* ነው። ርእሱ ከሞላ ጎደል ግሩም ነው። በንኡስ ርእሱ ላይ ግን አንባቢው ጥያቄ ሊኖረው ይችላል። ሊቀለበስ የተሞከረው ዴሞክራሲ የትኛው ይሆን? ኢህአዴግ ለተወሰነ ግዜ የፈቀደውን በቅድመ-ምርጫና በምርጫ ግዜ ለነበረው ሁኔታ ነው? ወይስ በቅንጅት የተመራውን የዴሞክራሲ እንቅስቃሴ? አንዳንዱም የቅንጅቱ እንቅስቃሴ ከእህአዴግ ግዚያዊና ለዘብተኛ የፖለቲካ አቋም (ፖሊሲ) ውጪ ማየት ስለማይቻል የትኛውን ዴሞክራሲ ይሆን ብሎ ማላመጥ ይችላል። ከነኚ ጥያቄዎች ውጪ ደግሞ አንዳንድ ምሁራንና ታዛቢዎች የዴሞክራሲ ባህል በኢትዮጵያ እንኳንስ መሠረቱ ሊጥልና ከናካቴው ስላልነበረ 'ሊቀለበስ የተመኮረው የኢትዮጵያ ዴሞክራሲ' ብሎ ማለት አይቻልም ሊሉ ይችላሉ። ይህ የኋላኛው ትንታኔ ከአጠቃላይና ግዙፍ (macro)

የምርት ግኑኝነቶችና ምጣኔ ሃብታዊ እድገቶች የተቆራኙ እንጂ በአነስተኛውና ጠባብ መልኩ (micro) በመንግስታትና ሰበስልጣናት ላይ ያተኮረ አይደለም። እኔም በመሠረቱ ይኸንን ትንታኔ አሳማኝ ሆኖ ስላገኘሁት የብርሃኑ ነጋ መጽሓፍ ዋናው ርእስ እንዳለ ሆኖ ንኡስ ርእሱ ግን ባይኖር ደስ ባለኝ ነበር።

ዴሞክራሲ እንደ ፖለቲካዊና ማሕበራዊ ባህረሃሳብ በኢትዮጵያ ላለማደጉ፡ እንድያውም ገና መልህቁን ላለመጣሉ ለሁላችን ግልጽ ሳይሆን አይቀርም። ለዚህም ይመስለኛል ዶ/ር ብርሃኑ በመጽሓፉ ውስጥ በገጽ 21 የድርጅትን አሰራር በሚመለከት ስያወራ "ብዙው ነገር ግን ከስብሰባ በፊት በቅስቀሳ የተወሰደ አቋም እንኳን በስብሰባ ላይ የተሻለ ምክንያት (argument) ከቀረበ በቀላሉ ይቀየር ነበር። ይህ እየተለመደ የሄደ ባህል የውሰጠ ድርጅት ዴሞክራሲን የማስፋት እድል ነበረው። እንዲህ ዓይነት የውስጠ ድርጅት ዴሞክራስያዊ ባህል በሌለበት ደግሞ ለሰፊው ማሕበረሰብ ያውም የፖለቲካ ሥልጣን ከያዙ በኋላ በአስተማማኝ መልኩ ማቅረብ ይቻላል ብየ አላምንም" ይላል። በምዕራፍ 1 ከገጽ 32 እስከ 40፡ ደራሲው የነጻነትና የዴሞክራሲ አስፈላጊነት ከዕድገት ጋር በማዛመድ አንዴ አመርትያ ሴንን ("ነጻነት የእድገትና የሥልጣኔ ግብም መሣርያ ነው") ቀጥሎም የዓለም ባንክ ጥናቶችን በመጥቀስ ተከራክሯል። እኔ የነጻነት አስፈላጊነት መሠረተ ሓሳብ የምስማማበትና የምደግፈው ነው። ነጻነት፡ ሌላው ቀርቶ ፈጣሪነትን ያጎለምሳል፡ ነጻነትን የመሰለ ፀጋ የለም። ሆኖም ግን ነጻነትና ምጣኔ ሃብታዊ እድገት የግድ የተዛመዱና የተቆራኙ አይደሉም። በሌላ አነጋገር፡ ነጻነት ወይም ዴሞክራስያዊ ባህል የእድገት ቅድመ-ሁኔታ ወይም መለክያ ሆነው መቅረብ አይችሉም። ይህ 'የእድገትና የነጻነት ግኑኝነት' አከራካሪና አወዛጋቢ ስለሆነ በመጠኑም ቢሆን ልገልጸው እፈልጋለሁ።

"ስለዚህም ነጻነት ያለው ሰውና ነጻ ሰዎች ያሉበት አገር በጣም ምርታማ ይሆናል ፈጣን እድገትም ይጎናጸፋል፡ ለዚህም ነው በእዝ ስርዓት ውስጥ ፈጣን እድገት የማይኖረው" ይላል ብርሃኑ (ገጽ 37-38)። ይህ ነው ዋና ችግሩ! ዶ/ር ብርሃኑ ኢኮኖሚስት ስለሆነ ከማንም በላይ ስለዚህ ጉዳይ በቅጡ ማወቅ ነበረበት። ዴሞክራሲና ነጻነት የምንመኘውና የምንናፍቀው ሥርዓት ነው። ነገር ግን ዴሞክራሲና እድገት በደረቅ ዝምድና (rough correlation) ማያያዝ አንችልም። በታሪክ እንደታየው የእድገት ቅድመ-ሁኔታዎች የምርት መጠንና የፖለቲካው ሥርዓት ፀባዮች (nature of political regime) ናቸው። የነዚህ ሁለት ቅድመ-ሁኔታዎችና ከእድገት ጋር ያላቸው ዝምድና፡ ወይም እድገትን በተመለከተ የሚጫወቱት ሚና ግን በቀላል አገር አቋራጭ የስታቲስቲክ አጋርነት (simple cross-country aggregate statistical correlation) የሚገለጽ አይደለም። ውስብስብ ነውና።

ከፍ ብሎ 'በታሪክ እንደታየው' ያልኩትን በቀላሉ ለመገንዘብ ያህል አንዳንድ ምሳሌዎች ልጥቀስ። ታላቁ ጴጥሮስ (Peter the Great) ሩስያን ዘበናይ ሕብረተሰብ ለማድረግ የሞከረውና የቻለው ዴሞክራስያዊ ሆኖ ሳይሆን፡ እንድያውም በአንጻሩ ፈላጭ ቆራጭ (ወይም ደግ አምባገነን) ስለሆነ ነው። የጥንት ቻይናውያን በ1450 ዓ.ም. ከማዝቀጣቸው በፊት እጅግ የምያስደንቅ የእርሻ ዘዴ፡ የእንስሳት አያያዝና እርባታ ዘዴ፡ መድፍ፡ የማግኔት ኮምፓስ፡ ወረቀት፡ ማተምያ ቤት፡ የጭነት ሰረገላ ወዘተ ሰርተው አልፈዋል። አሁንም ቢሆን ቻይና ውስጥ የተከሰተው ፈጣን ምጣኔ

ሃብታዊ እድገት በዓለም ደረጃ አድናቆትነት አትርፏል። እስከ አሁን ድረስ ግን የቻይና ሕዝብ የዴሞክራሲ ባህል የሚባል አልተጠጋውም። በአጠገባቸው የሚገኙ የምስራቅ እስያ አገሮችም በአምባገነን መንግስታት ቢገዙም ቅሉ ዴሞክራሲ ከሰፈነባቸው የደቡብ እስያ አገሮች እጅግ መጥቀው ሄዷል። የዚሁ ክስተት ሃቅነት በይበልጥ መገንዘብ ከፈለግን አንጻራዊ የተቋም ትንተና (comparative institutional analysis) ነው ማካሄድ ያለብን። ይህ የትንታኔ ዘዴ፡ ቀደም ብየ እንደጠቀስኩት፡ የፖለቲካ ሥርዓት ባህርይ በቀላሉ ለመገንዘብ ይረዳናል። ለምሳሌ በደቡብ ኮሪያ ፈጣን እድገት የተመዘገበው በፈላጭ ቆራጩ ፓርክ ሹንግ ሂ ነው። የፓርክ ሹንግ ሂ መንግሥት ዝም ብሎ በሥልጣን ላይ ቍጢጥ ያለ አምባገነን መንግስት ሳይሆን፡ በአገር ተቆርቋሪነትና ብሔራዊ ስሜት የእድገትን ጎዳና የቀየሰ ነበር። በዚሁ መንግሥት ስር ራሱን የቻለ የምጣኔ ሃብታዊ የንድፍ ተቋም (Economic Planning Bureau) ተቋቁሞ ነበር። በተመሳሳይ ደረጃ፡ ታይዋን ውስጥ፡ የእንዱስትሪ እድገት ቢሮ (Industrial Development Bureau) የሚባል ተቋም በእድገት ላይ ትልቅ ሚና ተጫውቷል። በተይም የችፍግ ፓርቲ አሰራር፡ ንድፎችና ፖሊሲዎችን ለድርድር ማቅረብ፡ መረጃን በማከፋፈልና በማቀናበር እጹብ ድንቅ በሆነ ፍጥነት ተግብሮታል ማለት ይቻላል። እዚህ ላይ ግልጽ መሆን ያለበት ግን እድገት ሊከናወን የሚችለው በአምባገነንነት ብቻ ሳይሆን መንግሥታቱ አርበኛና ተቆርቋሪ ሲሆኑም ጭምር ነው። ለዚህም ነው የፊሊፒኑ ማርቆስ፡ አምባገነንና አቆርቋዥ ስለነበረ፡ የገዛትን አገር፡ ፊሊፒን ድሃና ኋላቀር ሆና የቀረችው።

ከዚሁ ከነጻነትና እድገት ዝምድና ወጥተን ወደ ሌላ ዴሞክራሲ-ነክና ቁም-ነገር አዘል ነጥቦች መሸጋገሩ አስፈላጊ ስለሆነ፡ ዶ/ር ብርሃኑ በገጽ 60 የጠቀሰውን በአብዮታዊና በለዘብተኛ (ሊበራል) ዴሞክራሲ ደጋፊዎች ያለውን (ወይም የተካሄደውን) ክርክር ማየት ይኖርብናል። በአቀራረቡ ብርሃኑ የሊበራል ዴሞክራሲ ደጋፊና ጠበቃ ለመሆኑ በቀላሉ መረዳት ይቻላል። ቅድም እንደጠቀስኩት፡ ነጻነትና ዴሞክራሲን የመሰሉ ፀጋዎች የሉም። በዚሁም ረገድ የብርሃኑን አመለካከት እደግፈዋለሁ። ነገር ግን እንኳንስ አሁን ባለው የኢትዮጵያ አጠቃላይ የእድገት ደረጃ፡ በጣም መጥቀዋል (ከምጣኔ ሃብታዊና ከዴሞክራሲ አንጻር) የሚባሉ የምዕራብ አገሮች እንኳን የሊበራል ዴሞክራሲ ጽንሰ ሓሳብና ተግባራዊነት እየደበዘዘ ነው የሄደው። በቅርቡ በሞት የተለዩት ፕርዚደንት ፎርድ በሂወት እያሉ በላሪ ኪንግ የ ቲቪ ፕሮግራም ላይ በሰጡት ቃለ መጠይቅ "አመሪካ ውስጥ የግራና የቀኝ አክራሪነት አይሰራም፡ የመሃል ሰፋሪነት (centrist politics) ነው ብዙውን ግዜ አመርቂ በሆነ መንገድ ግቡን የሚመታው" ብለዋል።

ለነጻነትና ለዴሞክራሲ መጓጓትና በተግባር ማሳየት ግን ብዙውን ግዜ ላይገናኙ ይችላሉ። እንድያውም አንድአንድ ግዜ የስነ ልቦና ምኞት ከተጨባጭ ሁኔታ ጋር ሊጋጭ ይችላል። ለዚህም ይመስለኛል አንዳንድ ጸሓፊዎች እንደ ጆርጅ ላኮፍ የመሳሰሉ 'ነጻነት የውስጠ ወይራ አስተሳሰብ ግሩም አመለካከት ነው' ብለው የሚከራከሩት። የጸሓፊው መጽሓፍ *Whose Freedom? The Battle Over America's Most Important Idea* ነው። ቢነበብም ይረዳል።

በምዕራፍ ሁለት በኢትዮጵያ የዴሞክራሲ ግንባታ ሂደት ላይ የገጠሙ ችግሮች ወይም እንቅፋቶች ተዘርዝሯል። ከነዚሁ እንቅፋቶች አንዱ በ "ምሁራን አከባቢ

የበለጸገው …የጨለምተኝነት (cynical) ባህል ነው” (ገጽ 79)። በዚሁ ነጥብ ላይ ከሞላ ጎደል ከብርሃኑ ጋር እስማማለሁ፣ እኔም በበኩሌ የታዘብኩትና በአንዳንድ ጽሑፎቼ ላይ ያሰፈርኩት ነው። የሆኖ ሆኖ ግን ከጥቂት ወራዶችና ሓሞተቢሶች በስተቀረ የኢትዮጵያ ምሁራን ሳገራቸው ለኢትዮጵያ ከፍተኛ መስዋእትነት ስለከፈሉ ምስጋና ይገባቸዋል።

ከገጽ 88 እስከ 100 ደራሲው ‘ኢህአዴግና የግራ (የኮሚኒስት) ርእዮተ ዓለም’ እንዲሁም ‘ኢህአዴግና የዘውጌ ብሔርተኝነት’ አስመልክቶ ሂስ-አዘል በሆኑ ትንታኔዎች ገልጸታል። አንድ ያስቸገረኝ ነገር ቢኖር ግን ባሁኑ ግዜ ‘ኮሚኒስት’ የሚል አንጀባ መለጠፍ ባለፉት 16 ዓመታት በኢትዮጵያና በዓለም ዙርያ የተካሄዱትን ለውጦች ያለመገንዘብ ይመስለኛል። የዛሬ 20 ዓመት ቢሆን እንኳን ስለ ግራ ንቅናቄ ያላንዳች ችግር መናገርና መተንተን ይቻል ነበር። ያኔ የግራና የኮሚኒስት ሓይሎች በዓለም ዙርያና በኢትዮጵያ ውስጥ በሽበሽ ነበሩ። በዛን ሰዓት የግራ ርእዮተ ዓለም ያራመዱት የህወሓት (ወያኔ) ሰዎች ብቻ ሳይሆኑ የኢሕአፓ፡ ሜኤሶን፡ ደርግ፡ በመጠኑም የሕግሓኤ አባላትም ጭምር ነበሩ። ከ1991 ዓ.ም. ወዲህ ግን በዓይናችን የመሰከርነው ነገር ቢኖር (ሊቅነትና ፍልስፍናዊ ትንተና የማያስፈልገው) የሶቬት ኅብረትና የምስራቅ አውሮጳ ሾሻሊስት አገሮች እንደ ጤዛ ብን ብሎው መጥፋታቸው ነው። ርእዮተ ዓለማቸውም በዛው መጠን ተደርምሷል። ባንድ በኩል ይህ በምልዮኖች የሚቆጠሩ ሰዎች ያስገደለ ስርዓት መጥፋቱ ምርቃት ነው የምለው፣ ከሞትና ከስቃይም የጉልበት ብዝበዛና በከፊል ነጻነትን የሚሰጥ ሥርዓት (ካፒታሊዝም) ይሻላል። ስለሆነም አሁን ዓለም ባጠቃላይ (ቻይናም ሳይቀር) ወደ ካፒታሊስት ስርዓት እያመራ ነው። ይህ በእንዲህ እያለ ታድያ ኢህአዴግን ‘ኮሚኒሰት’ ማለቱ ትርጉም ያለው አይመስለኝም።

በዚሁ ምዕራፍ አንድ ቊምነገር የቀረበ ነገር ቢኖርና ብርሃኑም መመስገን ያለበት ግን በገጽ 107ና 108 የጠቀሳቸውን የነጻነትን ጥቅም በተመለከተ ነው። አንደኛ፡ “ነጻ ሕብረተሰብ መፍጠሩ ነጻ የምያወጣው ሁላችንንም ነውና!” ፣ ሁለተኛ፡ “የዴሞክራሲ ሥርዓት በመሠረቱ የፍቅርና የመቻቻል ፖለቲካ መነሻ ያደረገ ነው።” እነዚህ በጣም አስፈላጊ ጽንሰ-ሓሳቦች ብቻ ሳይሆኑ እንደ መምርያ ተጠቅመን ለአገራችንና ለሕብረተሰባችን ለወደፊት ዘለቄታ ያለው ፍትሓዊና ዴሞክራስያዊ ሥርዓት ለመገንባት የምንጠቀምባቸው መሆን አለባቸው። ይኸንን በተመለከተ በርካታ ጸሑፍ ስላቀረብኩ ብርሃኑም ሳያነባቸው አልቀረም የሚል እምነት አለኝ።

በዚሁ በዴሞክራሲ ግንባታ በኢትዮጵያ ላይ ብርሃኑ በጣም የተማመነ ይመስላል። ለምሳሌ በገጽ 112 እንዲህ ይላል፦ “ነጻና ዴሞክራስያዊ ሥርዓት በኢትዮጵያ መፈጠሩና ይህም ሥርዓት የሚገጥሙትን የተለያዩ ችግሮች ተቋቁሞ እያደረ የሚጎለብት ነጻ ሕብረተሰብ እንደሚፈጠር ምንም ጥያቄ የለውም…አሁን ባለንበት ሁኔታ በደምብ ግልጽ ያልሆነው “መቼና” “በምን ሁኔታ” የሚለው ነው። “መቼ” በኔ እምነት በጣም ከባድ ጥያቄ አይደለም፡ በቅርብ ግዜ የሚሆን ይመስለኛል።” የዶ/ር ብርሃኑ ተስፋ ከሞራልም አንጻር ብቻ ካየነው ለተስፋው ድጋፋችን መስጠት ይኖርብናል። ነገር ግን የዴሞክራሲ ግንባታ በቀጠሮ የሚሆን አይደለም፣ ተግባራዊነቱም ቢሆን በአውደ አዋርህ ማስቀመጡ የዋህነት ይመስለኛል።

በክፍል ሁለት ምዕራፍ 2፡ ደራሲው ከቅድመ-ምርጫ 97 የነበሩ ሁኔታዎች እስከ ዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ ግንኙነት ከገጽ 115 እስከ 148 በዝርዝር አስቀምጦታል፣ ለምን ጠንካራ ድርጅቶች እንዳልተፈጠሩም ዘርዝሮታል።

በምዕራፍ 4 ገጽ 158 “ሕዝቡ በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች ከምርጫው ጀምሮ ያገኘውን አንጻራዊ ነጻነት አላስረክብም፡ ተመልሼም የፍርሃት ሕይወት አልኖርም...” ማለቱን ብርሃኑ ይገልጻል። በዚሁ አቃቂር መጀመርያ ላይ ስለሚቀለበሰው ዴሞክራሲ ያቀረብኳቸውን ጥያቄዎች፡ አሁንም በተመሳሳይ “ሕዝቡ” በሚለው ላይ ጥያቄ ለማቅረብ ልገደድ ነው። ይህ ‘አንጻራዊ ነጻነት ያገኘው’ የተባለው የትኛው ሕዝብ ነው? የኢትዮጵያ ምልአተ ሕዝብ ወይስ የቅንጅት ደጋፊዎች? የኅብረት ደጋፊዎች? የኢሕአፓ/ሜኢሶን ደጋፊዎች? የኢህአዴግ ደጋፊዎች? ብዙ የቅንጅት ደጋፊዎች በምርጫው ለመሳተፋቸው ጥያቄ የለውም፣ ነገር ግን ከምልአተ ሕዝቡ የሌሎቹ ፓርቲዎች (የኢህአዴግ ሳይቀር) ደጋፊዎችም ነበሩ። እነዚህን ጥያቄዎች እርግፍ አድርገን በመተው፣ ደህና! ለክርክር ይመች ዘንድ የኢትዮጵያ ሰፊው ሕዝብ ነው እንበል። ግን ከዚሁ ጋር የተያያዘ ጥያቄ ባንዳፍታ ከፊታችን ይደቀናል፦ ‘አንጻራዊ ነጻነት’ የተገኘው በቅንጅት አርቆ አስተዋይነት፡ ብልሃትና ትግል ነው ወይስ ኢህአዴግ ባደረገው (ላጭር ግዜም ቢሆን) የለዘብተኛ መስተዳድር ፖሊሲ ወይም በፈቀደው (ላጭር ግዜም ቢሆን) የዴሞክራሲ መድረክ? ማንኛውም ጸሓፊ ወይም ገለልተኛ ታዛቢ ጥያቄውን መመለስ የሚችለው ሚዛን የጠበቀ፡ ፍትሓዊና ርትዓዊ ትንተና ስያቀርብ ብቻ ነው።

በገጽ 164 ዶ/ር ብርሃኑ የብሔርን ጥያቄ አስመልክቶ ተገቢና መልስ ማግኘት ያለባቸው ጥያቄዎች አቅርቧል። በአሁኑ ግዜ መቸም አማራ ጨቋኝ ብሔር ነው ብሎ ማለት ግዜው ያለፈበት ዘፈን መዝፈን ነው የሚሆነው፣ ግን ብርሃኑ እንዳስቀመጠው “በዚህ ላይ ጨቋኝ ማኅበረሰብ አማራው ነው ከተባለ በራሱ በኢህአዴግ ጥላስር ውስጥ የሚገኙ የአማራ ዘውግ አባላት ይኸንን ለመቀበል ይቸግራቸዋል” ብሎ መከራከር መጀመርያ ለምን? የሚል ጥያቄ ልያስከትል ነው። እኔ በኢህአዴግ አመራር ውስጥ ስላሉ አማርኛ ተናጋሪ ኢትዮጵያውያን መናገር አልችልም። እንዲሁ ስገምተው ግን ‘ማን ነው ጨቋኝ/ተጨቋኝ’ ለሚለው ጥያቄ መልስ መስጠት የሚቸግራቸው አይመስለኝም። ሁላችን ትዝ የሚለን ነገር ቢኖር (የኔ ትውልድ ማሌቱ ነው) ዋለልኝ መኮንን ነው እኮ የብሔርን ጥያቄ በግልጽ ያስቀመጠው፣ በኢሕአፓና ሜኤሶን የነበሩ የአመራር አባላት እኮ ናቸው የብሔር ጥቄ ፍትሓዊነትን ያራመዱት። ይህ የምያስፈራ ነገር አይደለም። መፍራትና መስጋት ያለብን የኢትዮጵያን ሕዝብ አንድነት የሚያፈርስ እንቅስቀሴ ሲካሄድ ብቻ ነው።

በገጽ 180 ብርሃኑ የኢህአዴግ አመራር አባላት “የነጻነት ምንነት በደንብ ስለማያውቁት” ይልና “የሰው ልጅ ለነጻነት ብሎ ሌላውን ቁሳዊ ጥቅሙን አሳልፎ ይሰጣል የሚል እምነት የላቸውም” ብሎ ይደመድማል። የኔ ሓላፊነት ምሁራዊ ትንተና ማቅረብ ስለሆነ ለመጀመርያው ዓረፍተ ነገር የኢህአዴግ አባላት ቢመልሱለት የተሻለ ይመስለኛል። የኋላኛው ዓረፍተ ግን ፍልስፍና-አዘልና አካራካሪም ስለሆነ፡ እኔም ልማርበት ስለምፈልግ፡ ለነጻነት ብለው በርካታ ሰዎች

በቅድመ-ግንባር የሚሰለፉና መስዋእት የሚሆኑም (altruism) ቢኖሩም ቅሉ፡ የሰው ልጅ ባጠቃላይ ግን ጥቅሙን የምያሳድድ ስለሆነ ይኸንን በተመለከተ ሰፊ ስነ ልቦናዊ ጥናት ማድረግ ያለብን ይመስለኛል። ብርሃኑም ራሱ ምናልባት የታዘበው ነገር ሊኖር ይችላል ብየ የምገምተው፡ የስራ ባልደረቦቹ (የቅንጅት አባላት) ሳይቀር መስዋእት ሳይሆን ክህደትን በማሳየት ልዩ አቅጣጫ ይዘው እንደተጓዙ ነው።

ደራሲው በገጽ 204ና 205 "ዴሞክራስያዊ ሥርዓት በመሰረቱ ሰላማዊ ነው" ብሎ ያቀረበውን ሙሉ በሙሉ የምቀበለው ነው። የማክልበት ነገር ቢኖር ግን ዴሞክራሲ በኢትዮጵያ ለመገንባት የኛ ሚና ምን መሆን አለበት? የሚለው ሲሆን፣ ሌላ ከዚሁ ጋር ተያይዞ የሚቀርብ ጥያቄ ደግሞ 'የዴሞክራሲ ስነሓሳብ ከአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ በማገናዘብ መተግበር እንችላለን ወይ? የሚለውን ነው። ብያንስ ብያንስ የዴሞክራሲ ጠበቆች ሆነን የምንቀርብ ግለሰቦች ራሳችንን በአርአያነት (ሽፍንፍንና ድብቅብቆሽ ፖለቲካ ሳይበክለን) ዴሞክራቶች ሆነን ስንቀርብ ነው። በቅድምያ ማድረግ የሚኖርብን ነገር ቢኖር የዴሞክራሲ ስነሓሳብና ታሪካዊ አመጣጡ በተመለከተ ሰፊ ትምህርታዊ ቅስቀሳ ማካሄድ አለብን። በዚሁ ረገድ የአስተሳሰብ ለውጥ ማምጣት ከቻልን ብቻ ነው ደግሞ በመጠኑም ቢሆን የዴሞክራሲ ባህል እንጭጭነት መትከል የምንችለው።

ከዚሁ ከሰላማዊ መንገድ ጋር በማያያዝ በገጽ 206 ቅንጅት 'የኢህአዴግን መሪ ድርጅት ህወሓትና የትግራይን ሕዝብ በፍጹም ለይቶ ማየት" የሚል አቋም እንደነበረው ብርሃኑ ይገልጻል። ቀጥሎም "ይህ ለእኛ የስልት ሳይሆን ከልባችን የምናምንበት ጉዳይ ነው" ይላል። መልካም አባባል ነው፣ የሚደገፍም ነው። ነገር ግን የቅንጅት መሪዎች ይኸንን የተቀደሰ መርሐ በግብር የተረጎሙት አይመስለኝም፣ አለዛ የቅንጅት ደጋፊዎች "ንብረት ወደ ቀበሌ፡ ትግሬ ወደ መቀሌ" ብለው አይዘምሩም ነበር። እውነቱን ለመናገር፡ የነዚህ ደንቃሮች አካኪ ዘራፍ ከንቃተ ኅሊና ዝቅተኛነት የመነጨ ነው፣ ለዚሁ ጉዳይም ቅንጅትን ሙሉ በሙሉ ሓላፊነት ማሸከም አይቻልም። በሌላ በኩል ግን ቅንጅት እንደ ድርጅትና የፖለቲካ ቡድን ጉዳዩን ለማጠፍና ለማስተካከል አስፈላጊ ትምህርታዊ ቅስቀሳ ያካሄደ አይመስለኝም። በሕቡእ ሆነ በገሃድ ያደረገው ነገር ካለ ግን እኔም ልማርበት (ልወቀስበትም ጭምር) እፈልጋለሁ።

በገጽ 209 ብርሃኑ ብሔር (ዘውግ ይለዋል) "የአመለካከት ጉዳይ አይደለም" ይልና፡ በጣም የገረመኝ ነገር ግን እኔ ከዚህ ቀደም ከጻፍኩት ጋር እጅግ በጣም የሚመሳሰል በዚህ መልክ ያስቀምጠዋል፦ "ማንም ሰው ከየትኛው ቤተሰብ፡ ከየትኛው ዘውግ፡ ወይም ከየትኛው የሰው ዘር ቀለም (Race) ወይም የትኛውን ጾታ ይዞ እንደሚወለድ መምረጥ የሚችለው ጉዳይ አይደለም።" አንባቢ እንድያውቀው ሁሉ እኔ የጻፍኩት (July 2, 2005) ደግሞ እንዲህ ነበር፦ "ማንኛውም ኢትዮጵያዊ የአንድ ብሔር አባል የሆነውን እንዳጋጣሚ መሆኑን፣ ኢትየጵያውነት ግን በታሪክ የተገነባ መሆኑን በቅጡ ይገነዘባል። ይህ በቀላል አማርኛ እንዲህ ማለት ነው፦ አንድ ግለሰብ ኢትዮጵያዊ የትግራይ ተወላጅ፡ የአማራ፡ ኦሮሞ፡ ጉራጌ፡ ሲዳማ ወዘተ አባል ሊሆን የቻለው እንዳጋጣሚ እንጂ ሆን ብሎ በእቅድ ከዚሁ ብሔር ልፈጠር ብሎ በመምረጥ አይደለም። እንዲህ ያለ ክስተት ተሰምቶም ታይቶም አይታወቅም፡ ለወደፊትም አይኖርም።" (www.africanidea.org/Doc5.pdf ወይም www.tecolahagos.com/Doc5.pdf

ተመልከት)። የዚሁ ጽሑፍ ይዘት እንደገና በ *ገድለ ጻድቃናት ዘኢትዮጵያ አክትሚል ወይ?* በሚል ርእስ ባቀረብኩት ሓተታ አስፍሬው ነበር።

የኔና የብርሃኑ የአስተሳሰብ መስመር (wave length) ሊገጥም ይችላል፣ ግን ከፍ ብየ እንደጠቀስኩት ብርሃኑ ጽሑፎቼን ሳያነብ አልቀረምና የከፊል ዝንጉነት በሽታ (selective amnesia) ተጠናውቶበት ይሆን የሚል ጥያቄ ሳሰላስል ቆይቻለሁ።

ከገጽ 213 ጀምሮ መጽሓፉ የቅንጅት ምስረታና ያጋጠመው ችግር ይገልጻል። የቀስተደመና ሆነ የቅንጅት ባስቸኳይ የተከናወነ ለመሆኑም በገጽ 223ና 224 ተገልጿል። በገጽ 230 ደግሞ ደራሲው "ቅንጅት በጥቅምት ማለቅያ ተፈጥሮ የምርጫው ዋና ዘመቻ ለመጀመር የቀረው ከሦስት ወር ያልበለጠ ጊዜ ነበር" ይላል። የድርጅቱ አጠቃላይ መዋቅር ሳያልቅ ተጣድፈው ወደ ምርጫው እንደገቡ ብርሃኑ በገጽ 231 ገልጾታል። የቅንጅት ዋና ድክመትም ይኸው ይመስለኛል። የነተሎ ተሎ ቤት ግድግዳው ሰንበሌጥ እንዲሉ ቅንጅቶች አስፈላጊውን የድርጅትና የመዋቅር ስራ ሳያከናውኑ ወደ ምርጫ መግባታቸው ዋጋውን ከፍሏል ማለት ይቻላል። በቅንጅት ዘንድ የድርጅት አሰራር ድክመት ስለነበረም ደራሲው በገጽ 232 እንዳስቀመጠው "ግለሰባዊና ግለ ድርጅታዊ ስሜቶች ውስጥ ለውስጥ ይንጸባረቁ ነበር" ፣ "በቂና መዋቅራዊ ትኩረት በመስጠት ለመመለስ ብዙ ለመሞከር ሳይቻል ቀረ" ፣ "ቅንጅቱ ያወጣቸውን የተለያዩ የውስጥ ሕጎች…እና መመሪያዎች ለመጠቀምና የሚነሱ ችግሮች በእነዚሁ መመሪያዎች መሰረት መፍታት አልተሞከረም።"

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ድክሞቶች ከምርጫውና ከኢህአዴግ ድርጅታዊ ጠንካራነት አንጻር ስናየው የገኘው ፓርቲ በርካታ ቅድመ-ጥቅሞች ነበረው ማለት ይቻላል። እንኳንስ በችኮላ የተለጣጠፈ ድርጅት፣ የብዙ ግዜ ልምድ ያላቸው ጠንካራና ኅብር ፓርቲዎች እንኳን የፖለቲካ ሥልጣን ሽምያና የግለሰቦች መናቆር (ውስጠ ደንብና ሕግጋትን በመጣስ) በቅንጅት ዙርያ ለመከሰቱ ግን የምያስደንቅ አይደለም። በገጽ 236 እንደተጠቀሰው የቀስተደመና አዲስነትና የኢደሊ ለምርጫው አለመዘጋጀት በደፈናው የቅንጅትን ድክመት የሚያሳይ ነው። ስለሆነም ቅንጅት ያካሄደው የፖለቲካ እንቅስቃሴ ስሜታዊና ቅጽበታዊ (spontaneous) እንጂ ረቂቅና ጥልቀት ያለው ድርጅታዊ አሰራር ያሳየ አይመስለኝም። ነገር ግን በችኩልነቱና በዝብርቅርቅነቱ ድክመት ብያሳይም ቅሉ አጠቃላይ የፖለቲካ ስትራተጂውና "የትግል" ስልቱ የጆርጅያ ቅጽበተዊ አብዮት የተከተለ እንጂ በአቋራጭ ሥልጣን ለመያዝ ብቻ የተነሳ ኃይል አልመሰለኝም።

በገጽ 238 የፓርቲ አባሎች (ግለሰቦች) የሞያና የትምህርት ችሎታቸውና መዓርጋቸውን አስመልክቶ "ተራ ማጭበርበሮች" እንደሚደረጉ ብርሃኑ ይጠቅሳል። እኔ በበኩሌ ስለተጠቀሰው ግለሰብ የማውቀው ነገር የለም፣ ግን ብዙ ኢትዮጵያውያን (በተላይ በስደት የሚገኙ) የሌላቸውን የትምህርት ደረጃ አለኝ ብለው በመዋሸት፣ አንዳንዱ ደግሞ ከውሸት ኮሌጆችና ዩኒቨርሲቲዎች በኢንተርኔት አማካኝነት በመግዛት በውሸት ድግሪያቸውን ሲቦርቁ ስላየሁ ጥናትና ምርምር በማካሄድና ውሸቱን በማጋለጥ እኔ በምመራው ኢንስቲትዩት (የአፍሪቃ ልማትና ትምህርት ተቋም) አማካኝነት ወብሳይት ላይ ለጥፈነው ስለነበር አንባቢ ይማርበት ዘንድ

በማለት የሚቀጥለውን የኢንተርነት የአድራሻ መስመር ለመጎብኘት እጋብዘዋለሁ፣ www.africanidea.org/africans.html ርእሰ-ነገሩ Africans: Be Ware of Fake Universities and Fraud Credentials ነው።

በገጽ 243 አሁንም ቢሆን በቅንጅት አመራር ዘንድ የጅብ ችኩል ጠባይ ለመታየቱ ከሚቀጥለው ሓተታ መገንዘብ ይቻላል፦ "...በእነኚህ ድርጅቶች ውስጥ የተንሰራፋው የድርጅት ውስጥ ባሕል በፍጹም ጤናማ እንዳልሆነ፡ ስለሆነም ከተሻገርን በኋላ በተቻለ ፍጥነት ድርጅቶቹን ማዋሃድና ቅንጅቱን ከአራት ፓርቲዎች ወደ አንድ ፓርቲ መቀየር ምንም አማራጭ የሌለው መንገድ መሆኑን ተገነዘብን" (የተሰመረበት የኔው ነው)።

አንድ ፓርቲ ለማድረግ መሞከሩ አስፈላጊና ርትዓዊ ነው፣ ግን "በተቻለ ፍጥነት" የሚገነባ ፓርቲ ብቁና ዋስትና ያለው ሊሆን አይችልም። ሰርገኛ መጣ በርበሬ ቀንጥሱ ነው የሚሆነው። በዚሁ ላይ በተጨማሪ መታየት የነበረበት የልዩ ልዩ ድርጅቶች መሪዎች የፖለቲካ ንቃት፡ የአመራር ችሎታና የመስዋእትነት ዝጉጅነት ነው። መስዋእትነት ለመሞት መዘጋጀት ብቻ ማለት አይደለም። በአንድ ድርጅት ውስጥ ታታሪነትና የመርሕ ጽናትም ማሳየት እንደ መስዋእትነት መቆጠር አለበት። የዚሁ ተቃራኒ ደግሞ ክህደትና ከትግል አውድማ መፈርጠጥ፣ በቅድመ ግንባር የተሰለፉትን ግለሰቦችንም አሳልፎ መስጠት ይሆናል። ምናልባት አሁን ይኽ በፖሊቲካ ዙርያ የሚንጸባረቀው ውስብስብ (እንድያውም የሚዘገንን) የሰው ጸባይ ለብርሃኑና ከእርሱ ጋር ቃሊቲ ውስጥ ያሉት ጓዶቹ እያደረ ሳይከሰተላቸው አይቀርም የሚል ግምት አለኝ።

የቅንጅት ድክመት ግን በዚሁ የሚያልቅ አይመስልም። "ቀስተደመና ቅንጅት የማቋቋም ዓላማውን ተግባራዊ ለማድረግ ከመጀመሩ በፊት ባደረጋቸው ሰፊ ውይይቶች በመጀመርያ የዚህን የአማራጭ ራዕይ እጥረት (vision deficit) መስፈን እንዳለበት ነበር የተገነዘበው" ይላል ብርሃኑ። መቸም ማንኛውም የሰው ልጅ ከአርቆ አስተዋይነትና ራእይ ጋር አይፈጠርም። ቅንጅትም እንደ ማንኛውም ፓርቲ ይኸንን እጥረት ልያሳይ ይችላል፣ ግን ራእይ በአመራር ደረጃ በተለይ ወሳኝ ሚና ስለሚኖረው የዚሁ ጉድለት ያለው የፖለቲካ ድርጅት የኋላ ኋላ እንደ መናጢ ነጋዴ መክሰሩ አይቀርም።

በምዕራፍ 6 መጀመርያ ገጽ (259) ላይ ደራሲው "የግንቦት 97ን ምርጫ 'ማን ያቸንፋል' ከሚለው ጠባብ የድርጅት ፍላጎት በላይ አክብዶ ያየው ነበር" ብለዋል። ይኸንንም ያለበት ምክንያት "ምርጫው ኢትዮጵያ ወደ ዴሞክራስያዊ ሥርዓት እውነተኛ ሽግግር ማድረግ አለማድረጓን የምታሳይበት...ለዴሞክራሲ ሥርዓት አስፈላጊ ነው የሚባለው የተቋማት ነጻነት የሚረጋገጥበት ካልሆነ" እኔ እነደገባኝ ከሆነ ጥያቄው የመሸነፍና የማሸነፍ አይደለም ነው። እኔ እንደማውቀው ግን፡ በፖለቲካ ሳይንስም ሀሁ ነው የምንለው፡ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ የሚወዳደረውና የሚታገለው ለማሸነፍና የመንግስት ሥልጣንን ለመጨበጥ ነው። ይህ የመቅድም ግቡ ነው። መሰረታዊ ለውጥ ለማምጣት ሆነ በኢትዮጵያ የዴሞክራሲ ግንባታ ለማረጋገጥም እኮ በከፊልም ቢሆን ሥልጣን መያዝ አለበት። አለዛ ምን ይዞ ጉዞ? ነው የሚሆኖው። በተጨማሪም ከዚሁ ጋር አያይዘን ሌላ ጥያቄ

ማንሳት እንችላለን። የምርጫ ውድድር ግብ ለማሸነፍ ካልሆነማ (ወይም ቀደምት ቦታ የማይሰጠው ከሆነ) ለምን ታድያ ቅንጅቶች ያን ያህል በርካታ የፓርላማ ወንበሮች አቸንፈው ስያበቁ ወደ ብሔራዊ ሸንጎው አልተቀላቀሉም?

ከገጽ 301 እስከ 303 ደራሲው ከቅድመ-ምርጫ የነበሩትን ክርክሮች በማውሳት ኢሕአዴግ ክርክር እንዲኖር መፍቀዳቸው፡ የቅንጅት ባልደረቦቹ ግን እንደተቃወሙትና በውሳኔአቸው "ፍጹም ደስተኛ" እንዳልነበረ ይገልጻል። በመጽሓፉ በዚህ መልክ አስፍሮታል፦ "...በረከት በከረረ መልኩ ይህ ውይይት ቢደገምና ለብዙ ሕዝብ በሚደርስ መልኩ ማታ ማታ ከዜና በኋላ (prime time) ቢተላለፍ ጥያቄውን ለማጥራት ይጠቅማል ብሎ እንደምያስብ ገለጸልኝ።... ጉዳዩን ለስራ አስፋጻሚ አቅርቤ በሰፊው ከተወየየንበት በኋላ በመርሕ ደረጃ ክርክሩን እንደምንቀበል ግን የመጨረሻ ውሳኔ ከመስጠታችን በፊት የክርክሩ አቀማመጥ ላይ በዝርዝር መስማት እንደምያስፈልግ..." ካለ በኋላ እንደገና ይቀጥልና "ጉዳዩን በማግስቱ ለሥራ አስፈጻሚ ስናቀርብ ግን እኔ ከገመትኩት በላይ ተቃውሞ ገጠመኝ። ብዙው የሥራ አስፈጻሚ አባላት በቀጥታ ስርጭት ካልሆነ በቀር...ከቀጥታ ስርጭት ውጪ በምንም ዓይነት መሳተፍ የለብንም ብለው ወሰኑ።"

ነጻና ፍትሓዊ ምርጫ አስመልክቶ ደራሲው በገጽ 392 ትክክለኛና ርትዓዊ በሆነ መንገድ አስቀምጦታል። የዴሞክራሲ ሥርዓትና ሂደት አንዱ መለክያው ነጻና ፍትሓዊ ምርጫ ሲካሄድ ነው። ይኸንንም አስመልክቶ በተደጋጋሚ በጽሑፎቼ አስፍርያቸዋለሁ። ለውይይት እንዲመችና አንባብያን በዚሁ ረገድ ጠለቅ ያለ ግንዛቤ ይኖራቸው ዘንድ፣ ከሌሎች ተመክሮዎችም መማር ስላለብን፣ የሚከተለውን ርእሰ-ነገር እንድያነቡ እጋብዛቸዋለሁ፦ *What Africa Can Learn From American Democracy & Election 2006* www.africanidea.org/what_africa.html

በገጽ 395 ዶ/ር ብርሃኑ "ቅንጅት ምርጫ ውስጥ ሲገባ በምርጫ ቦርድ ላይ ብዥታ ኖሮት አይደለም" ካለ በኋላ፡ ብዥታውን ለማብራራት "...የቅንጅት አባል ድርጅቶች ከተደራደርን መደራደር ያለብን ከመንግሥት ጋር እንጂ ከኢህአዴግ ጋር አይደለም ብለው አንሳተፍም ሲሉ በዋናነት ያነሱት የምርጫ ቦርዱን ጉዳይ ነው" ይላል። በእርግጥ ፓርቲና መንግሥት አንድ አይደሉም። የገዢው ፓርቲ ግን የመንግሥት አውታሮችን መቆጣጠሩ ብቻ ሳይሆን በማንኛውም የመንግሥት ፖሊሲ ላይ ትልቅ ሚና ከመጫወቱም በላይ ጫና ማድረግም ስለሚችል ከፓርቲ ጋርም (በተለይ በሦስተኛ ዓለምና ዴሞክራሲ ባልተጠናከረበት አከባቢ) መደራደር አስፈላጊ ሊሆን ነው። የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ኃይሎች ይኸንን ሓቅ ከቍጥር ማስገባት ይኖርባቸዋል።

በገጽ 396 ደራሲው "ፈረንጆች ለተቋማት ከበሬታ አላቸው" ያለውን እውነትነት የምያንጸባርቅ ቢሆንም ቅሉ ንቃተ ኅሊናቸው ዝቅተኛ ለሆኑ የሕብረተሰብ አባላት በተለየ መልክ (የፈረንጆች ልዕልና) ሊገነዘቡት ስለሚችሉ ፈረንጆች ለምን የሕግ ልዕልና እንደምያከብሩ ከሁለንተናዊ ዕድገትና የመጠቀ ምጣኔ ሃብታዊ ሥርዓት ጋር በማጣመር መግለጹ ያሻል። በተቻለ መጠን ደግሞ ምሁራን የምንባል ሰዎች የምዕራብ አገሮችና የአፍሪቃ አገሮች ባናወዳድር የተሻለ ነው። ልዩነታቸው እጅግ በጣም ግዙፍ ነውና። እንደ ኢትዮጵያ የመሰሉ ታዳጊና ድሃ አገሮች መወዳደር

ያለባቸው ከመልካም እርምጃ ካሳዩት የአፍሪቃ አገሮች እንደ ቦትስዋና (በኢኮኖሚና በፖለቲካ ረገድ) ወይም ሌሎች የጦፈ የእድገት ዘመቻ በማካሄድ ላይ ያሉት እንደ ህንድ፡ ብራዚልና ቻይና ነው።

በገጽ 415 አንድ በጣም ያሳዘነኝ ነገር ብርሃኑ አስፍሮታል። ይኸውም በምርጫው ግዜ የአፍሪቃ ኅብረት ታዛቢዎች "በሂደቱ የሚደረገውን ነገር" መከታተል አለመቻላቸው ነው። እስከ አሁን ድረስ አፍሪቃኖች የራሳቸውን ጉዳይ መምራት አልቻሉም ። በጣም የምያሳዝነው ደግሞ የአውሮጳ ኅብረት ታዛቢዎች ከአፍሪቃ አንድነት ታዛቢዎች በላይ የኢትዮጵያን የምርጫ ውዝግብና ውጤት ማወቃቸው ነው። አውሮጳኖች አሁንም ቢሆን በአፍሪቃ ጉዳይ ላይ የበላይነት ስላላቸውና የአፍሪቃ መሪዎችም በገዛ ራሳቸው ስለማይተማመኑ ፈረንጆች በኛ ላይ (ወይም በጉዳያችን ላይ) እብሪትና ንቀት ብያሳዩም እንኳ 'እንዲህ ነሽና!' ብሎ የሚጋፈጥ የአፍሪቃ መሪ የለም። ስለዚህ እንደተለመደው እነሱ የኛ የፖለቲካ የእልፍኝ አስከልካይና የፕሮቶኮል ወሳኝ ሆነው ይቀጥላሉ፣ እኛ ደግሞ ተንበርካኪና (ወቸ ጉድ!) ተመጽዋች ሆነን እንቀጥላለን።

ከገጽ 428 እስከ 453 ብርሃኑ የምርጫውን ውጤት አስመልክቶ ከተቃዋሚ ድርጅቶች ጋር የሚኖራቸውን ግኑኝነት፡ ከመንግሥት ጋር የምያደርጉት ድርድር እንዲሁም ምርጫ በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት ማቀዳቸውና መሞከራቸውን ሰፋ ባለ መልክና በግልጽ አስቀምጦታል።

በገጽ 458 ግርጌ ማስታወሻ ላይ ደራሲው ከልደቱ ጋር የነበራቸውን ልዩነት አስመልክቶ ካተተ በኋላ "ሕዝብ የሚለውን ከውሳኔ በፊት ማወቁ ይጠቅማል እንጂ አይጎዳም። ይህ ደግሞ በምንም ዓይነት 'መሪነትን' አሳልፎ መስጠት አይደለም" ይላል። እነ ብርሃኑ "የሕዝቡን ስሜትና ፍላጎት ለመለካት" ሕዝቡን በቀጥታ ስያነጋግሩት "ውሳኔያችንን ደግፋችሁ ከጎናችን ትቆማላችሁ ወይ?" የቅንጅቱን አመራር ታምኑታላችሁ ወይ?" ብለው መናገራቸው (ገጽ 460) ደራሲው ይጠቅሳል። እንዴ ሕዝቡ ለቅንጅት ከመረጠ እኮ በነሱ ላይ እምነት አለው ማለት ነው። ቅንጅት ይህ 'አዲስ ዴሞክራሲ' የሚለውን አጉልና ባዶ ተስፋ የሚሰጥ ካልሆነ በስተቀረ፡ ከዚህ ቀደም በተለያዩ ጽሑፎቼ እንደገለጽኩት ዴሞክራሲ በሕዝብ ተወካዮች ነው ሊተገበርና ግቡን ሊመታ የሚችለው። አለዛ ሕልምና ቅዠት ውስጥ መነከር ነው የሚሆነው።

በተቃዋሚ ፓርቲዎች አለመተማመን መኖሩን የምያሳይ በገጽ 462 ብርሃኑ በዚህ መልክ ያስቀምጠዋል፦ "...በአመሪካ ሁለተኛ ጉባኤውን ያደርግ የነበረ ኅብረት እኛን ምንም ሳያማክር ቀንና የትግሉን ዓይነት ቆርጦ ለመስከረም 22 ቀን ሰላማዊ ሰልፍ በአዲስ አበባና በሌሎች ከተሞች መጥራቱን ከግል ጋዜጦች አነበብን።" ይህ በተቃዋሚ ኃይሎች መሃል መረጃ መቀያየርና አብሮ መስራት፡ ከዛም አልፎ የጋራ ስተራተጂ መቀየስ እንዳልነበረ ያሳያል። ምክንያቱም፡ እንኳንስ በቅንጅትና በኅብረት መሃል በቅንጅት ውስጥ እንኳን መተማመን እንዳልነበረ ከብርሃኑ መጽሐፍ በቀላሉ መረዳት ይቻላል።

በገጽ 473 የቀስተደመናና የኢ.ዴ.ሊ. ስብጥር ውሳኔዎች ከተተቸ በኋላ የእኩልነት መርሕ መሰረት በማድረግ፡ ብርሃኑ ሁለቱ ድርጅቶች እኩል መቀመጫ እንዲሰጣቸው ሓሳብ አቅርቦ እንደነበር ይገልጻል። ይህ ሐሳብ ትክክለኛና ፍትሓዊ፡ ብሎም አስታራቂና አንድነትን የምያጸና ሓሳብ ነው። ግን በዚሁ ገጽ መጨረሻ ላይ የሰፈረው እጅግ የምያሳስብ ነው፦ "ግን ከአጀማመሩ አዲስ የመጡት ሰዎች ምንም ሳይሰሩና ሳይደክሙ የበላይነትን ያዙ የሚለውን ሁኔታ..." የሚለውን አመለካከት ከሥልጣን ጉጉትና ፍላጎት የተቆራኘ ሆኖ በቀላሉም ከኢትዮጵያውያን (ፌውዳላዊ) ስነልቦና የሚጠፉ አይደለም። ለመፍትሔውም ጠለቅ ያለ ጥናትና ምርምር ሊያስፈልገው ነው። በግዚያዊ መልክ ግን የኢትዮጵያ የፖለቲካ ድርጅቶች አወቃቀር ሆን ተብሎ ብቃት ያላቸው መሪዎች የምያፈሩበት ልዕለ-ቅርፅ እንዲኖራቸው ብንገነዘብም ቅሉ፡ በውክልና ደረጃ ግን ጾታ፡ ብሔር፡ ኃይማኖት፡ ዕድሜ፡ አዲስና የቆዩ አባላት ወዘተ እንድያካትቱና የያንዳንዱ ድርጅት ፍላጎት እንድያረኩ መሆን አለባቸው።

በገጽ 477-78 ብርሃኑ በኢ.ደ.ፓ-መድህን ማእከላዊ ምክር ቤት ምርጫ መካሄዱንና አምስት ሰዎች መመረጣቸውን ካወራ በኋላ በጉዳዩ እንደተገረመና ቅር እንዳለው ይገልጻል። በተጨማሪም፡ "የተረዳነው ነገር" ይላል ብርሃኑ "እነዚህ ልጆች እነሱ የማይቆጣጠሩትን ድርጅት ለማወክ ወደኋላ እንደማይሉ ነበር።" እንዲህ ከሆነማ ቅንጅት እንዴትስ ብሎ አገርን መምራት በቻለ ነበር፡ የፈለገውን ሥልጣን ቢሰጠውም እንኳን! በድርጅቱ የነበሩ ልዩነቶች በጣም ግዙፎች ከመኖራቸውም በላይ በችኮላና በጥድፍያ የተከናወኑ የፖለቲካ ውሳኔዎችና ድርጅታዊ ሥራዎች ስለታከሉባቸው ቅንጅት የኢሃአዴግ ብትር ሳይመታውም በገዘ ራሱ ይበላ ነበር። ከገጽ 503 እስከ 518 እና ምዕራፍ 12 (ገጽ 519) የቅንጅት ፓርላማ ውስጥ መግባት አለመግባት የሚለውን በዝርዝርና በሰፊው ቀርቧል። በገጽ 503 ለምሳሌ "ተቃዋሚዎች ፓርላማ ካልገቡ ግን የመንግሥቱ ትክክለኛነት ጥያቄ ውስጥ ይገባል፣ መንግሥት የሚወስደው እርምጃ አለመረጋጋት ሊፈጥር ይችላል...ስለዚህ አደጋውን ለመከላከልም ቢሆን ተቃዋሚዎች ፓርላማ እንዲገቡ መግፋት የግዜው ፖሊሲ ነበር" ይላል። ፓርላማ መግባቱ ግን መንግሥት ገና ለገና እርምጃ ይወስዳል ከሚል ሳይሆን በመርሕ ደረጃና ከተገኘው አንጻራዊ ድል (ቅንጅቶች ያቸነፏቸውን ወንበሮች) ጋር በማመዛዘን ከታየ በኋላ ቅንጅቶች ወደ ፓርላማው መግባት ነበረባቸው። ይኽንን መሰረት በማድረግ ነው ደግሞ እኔ በበኩሌ ቅንጅቶች ወደ ፓርላማው እንዲቀላቀሉ፣ ከተቻለም ሃገራዊ የእርቅ ድርድር ተደርጎ ጣምራ መንግሥት እንዲቋቋም በጽሑፍ ያቀረብኩት፦ *Coalition Government and Comparative Politics: Meanings for Ethiopia* በ [www.africanidea.org/coalition_government.html](http://www.africanidea.org/coalition_government.html) ተመልከት።

በገጽ 504 እንደተገለጸው "ዶ/ር መራራ በግልጽ እንዳስቀመጠው በመርሕ ደረጃ ውሳኔ ቢሰጡ በርካታ ተመራጮቻችን የምያስከዳቸው ይሆናል። ዶ/ር በየነ ቀድሞዉኑም 'ብልጥ ልጅ የያዘውን ይዞ ያለቅሳል' በሚለው ንግግሩ ፓርላማ እንደሚገባ ጠቁሟል።"

የዶ/ር በየነ የ'ብልጥ ልጅ' ቢሂል ላክልበትና የዛሬ 29 ዓመት (ይመስለኛል) ከቆላ ወገራ ተነስተን ወደ አርማጭሆና ጭልጋ (ጎንደር ክፍለሃገር) በምንቀሳቀስበት ግዜ፡

ሕዝቡን ስናስተምር አንድ ግርማ ሞገስ ያላቸው ብልህ ሽማግሌ ከኔ ጋር የተቀያየሩትን ሓሳብ ላጫውታችሁ፦ "እናንተ ልጆቻችን ሃገራችን ኢትዮጵያን ለመቀየርና ለማበልጸግ እንደምትታገሉ ለሁላችን ግልጽ ነው፣ እንደግፋቹሃለን። መሬት ላራሹ ብላችሁ እንደተነሳችሁም እናውቃለን፣ በዚሁ በአካባብያችን ደግሞ መሬትን ለመሸንሸን እቅድ እንዳላችሁ ሰምተናል፣ ይኽ ግን ለግዜው ቢቆይ የተሻለ ይመስለኛል" ካሉ በኋላ ንግግራቸውን በማቋረጥ "ለምን" ብየ ጠየቅኳቸው። መልሱም "ሥርዓቱን ለማጥፋት እኮ ሥርዓቱን ይዞ ነው" ነበር። ይኸን የቀሰምኩትን ትምህርት በ1995 በጻፍኩት መጽሓፍ (Ethiopia: The Political Economy of Transition) ውስጥ ጠቅሼዋለሁ። ለወደፊት በፖለቲካ ዙርያ የሚንቀሳቀሱት ኢትዮጵያውያን ይኸንን ተመሳሳይ ብልሓት ይዘው መንቀሳቀስ ይኖርባቸዋል።

በገጽ 505 የቅንጅት ፓርላማ መግባት አለመግባት በሚለው ጥያቄ ላይ የተቀነባበረ አለመኖሩን በዚህ መልክ ተገልጿል፦ "እንጂነር ኃይሉ ለህክምና በሄደበት በአመሪካ ከኢትዮጵያውያን ጋር ባደረገው ውይይት ከነበረበት ግፊት የተነሳ ቅንጅት ገና ውሳኔ ሳይሰጥ "ቅንጅት ፓርላማ አይገባም" ሲል ተናግሮ አዲስ አበባ የነበረውን አመራር በጣም አበሳጭቶ ነበር።" የእንጅነር ኃይሉ አቋም (ወይም ልሳናዊ እንቅፋት) 1) የቅንጅት የአሰራርና የማቀነባበር ድክመት፡ 2) የአመራር ብቃት አለመኖሩን፡ ያሳያል።

ቅንጅት ማድረግ የነበረበት (በገጽ 510 እንደተጠቀሰው) "ያገኘውን የሕዝብ ተቀባይነት ይዞ በፓርላማ ውስጥ የሕዝቡን ጩኸት እያሳማና አዲስ አበባን እያስተዳደረ ለሚቀጥለው የወረዳና የቀበሌ ምርጫ ቢዘጋጅ ይሻላል፡"

ደራሲው በገጽ 528 በቅንጅት "ድርጅታዊ ድክመት" ላይ ከተቸ በኋላ በሚቀጥለው ገጽ ደግሞ "ቅንጅት እንደ ድርጅት ግን ክፍትና ግልጽ ድርጅት ነው" ይላል። በኔ አመለካከት 'ክፍትና ግልጽ' ድርጅት ጥቅምም ጉዳትም አለው። ባደጉና በበለጸጉ አገሮችና ሕብረተሰቦች ክፍትና ግልጽ መሆን ያዋጣል፣ ኋላቀርና ታዳጊ በሆኑ አገሮችና ዴሞክራሲ ባልሰፈኑባቸው ሕብረተሰቦች ግን፡ ፍትሕና ርትዕ እንዲሁም የሕግ ልዕልና ስለማይኖር፡ በከፊል ግልጽ የመዋቅርና የድርጅት አሰራር፡ በከፊል ደግሞ በሕቡእ ፖለቲካ ስራዎችን ማካሄድ የምያዋጣ ይመስለኛል። ይህ ንድፈ-ሓሳብ ግን የአመራርና የድርጅት ጠንካራነት (እንዲሁም የርእዮተዓለምና የፖሊሲ አንድነት) በመጠኑም ቢሆን ለምያስመዘግቡ ድርጅቶች ብቻ ነው የሚሰራው። ከዚሁ 'ክፍትና ግልጽ' ጽንሰ-ሓሳብ ጋር የተያያዘም በገጽ 529 መጨረሻ ሁለት መስመሮች ላይ ብርሃኑ "በምንም ደረጃ ያለ ሰላይ በቅንጅቱ ውስጥ ምንም ምስጢር እንደሌለ ስያውቅ ይተወናል፡ መከላከያችንም እሱ ነው የሚል ጥልቅ ስሜት አለን" ይላል። ይህ የፖለቲካ የዋህነትን ነው የምያንጸባርቀው። ድርጅቶች እኮ ሚስጢር እንዳይወጣ ብቻ አይደለም በጽናት የሚከላከሉት። አጠቃላይ የፖለቲካ ስልትና ንድፎችም ጭምር በይፋ እስከሚወጡ ድረስ ተንከባክቦ መያዝም ጭምር ነው። አለዛ 'ለምሳ ያሰቡን ለቍርስ አረግናቸው' ዘይቤ እውን ሊሆን ነው ማለት ነው።

ከገጽ 562 እስከ 564 ደራሲው በኢህአዴግ ሰዎች አንጎል ውስጥ ገብቶ እንደ መመርመርና አስተሳሰባቸውን እንደማንበብ አድርጎ ይቀርብና በድራማ መልክ "ይህን ትንተና በኢህአዴግኛ ላስቀምጠው" ካለ በኃላ "ፈረንጆች እኛ ጥቁሮችን

በተለይ አፍሪካውያንን ስለሚንቁን (ፊት ለፊት ባያሳዩትም) በዴሞክራስያዊ ሥርዓት ግንባታ ዙርያ ከእኛ ብዙም አይጠብቁንም" ይላል። ይህ ልበ-ወለድ ድራማ የኢህአዴግ አመለካከት ልያንጸባርቅ ላያንጸባርቅ ይችላል፣ የፈረንጆች አመለካከት በተመለከተ ግን ከእውነትነት የራቀ አይደለም። ፈረንጆች በጥቁር ሕዝቦች ላይ ያላቸውን አመለካከት በቀጥታም በተዘዋዋሪ መንገድም ማሳየት ብቻ ሳይሆን ከጥቅማቸው ጋር የተያያዘ ፖሊሲ ማራመድም የተካኑበት ጉዳይ ነው። አመሪካ በተለይ የሃሚልቶን (ከመስራች አባቶች አንዱ) ስትራተጂ (ብሔራዊ ጥቅምን ማስቀደም) ስለምትከተል 'የዘሌቄታ ጥቅም እንጂ፣ የዘሌቄታ ጓደኛ የለንም' ብላ ለዓለም ማሕበረሰብ ካስታወቀች ቆይታለች። የሰው መብትና የዴሞክራሲ ጥያቄዎች ለይስሙላ ይነሳሉ እንጂ ምዕራባውያን ጥቅማቸው እስካልተነካ ድረስ የጭራቅና የአምባገነን መንግሥታት ማቀፋቸውን ሁላችን የምንገነዘበው ይመስለኛል። የሆኖ ሆኖ ግን፣ ግራም ነፈሰ ቀኝ፣ ኢህአዴግ በዲፕሎማሲ መስክ ላይ ከአውሮጳ አንድነት ይሁን ከአመሪካ መልካም ግኑኝነት ስላለውና ከነሱም ድጋፍ (የዲፕሎማሲና ቁሳዊ) ስለምያገኝ የፖለቲካ የበላይነት እጀታ ይኖሮዋል ማለት ነው። ወደድንም ጠላንም የፖለቲካ አንዱ መልኩና ፀባዩ ደግሞ ይኸው ነው።

በገጽ 569 ብርሃኑ የፓርላማ መቀመጫዎችን አስመልክቶ -- የያዙትን ይዘው እንዲገቡና አርፈው እንዲቀመጡ -- አንድ የኢህአዴግ ባለሥልጣን እንዳስፈራራው ከገለጸ በኋላ በዚሁ ገጽ የግርጌ-ማስታወሻ "በሌላ አነጋገር ቅንጅት ለመርህ ይቆማል ብለው አልገመቱም" ይላል። የሥልጣን እብሪትና ትዕቢት (arrogance of power) ብዙውን ግዜ ሥልጣን በጨበጡ ባለሥልጣናት ዘንድ የሚንጸባረቅ ነው። ለእንዲህ ያለ የፖለቲካ ሃው ግን በመርሕ ብቻ መጋፈጥ አይቻልም፣ መርሕና ፖለቲካ አንድ አይደሉም፣ እንድያውም ብዙ ግዜ ይጋጫሉ። ስለሆነም መርሕን በመከተል ብቻ ግቤን እመታለሁ ብሎ ማሰብ የዋህነት ነው።

በገጽ 572 "የአመለካከትና የርእዮተዓለም ቀውስ" ከከበርቴ ሥርዓት ጋር በማገናዘብ ደራሲው ይጠቃቅስና "የከበርቴው ሥርዓት የእድገት መሰረቱ ሕዝብ ነው…ሕዝብ ይህን የእድገት ሚናውን በአግባቡ እንዲጫወት ደግሞ ነጻ መሆን አለበት" ብሎ ይደመድማል። ያለ ሕዝብ መቸም የኢኮኖሚም ሆነ የፖለቲካ ተግባሮች ማከናወን አይቻልም። በኔ አስያየት ግን "ሕዝብ" ከከበርቴ እድገት መሰረት ጋር አያይዞ መጥቀሱ ይኸን ያህል ጠቀሜታ ያለው አልመሰለኝም። እኔ እስከማውቀው ድረስ የካፒታል ክምችት (የከበርቴ ሥርዓት በእንጭጭነቱ) ራሱን የቻለ ታሪካዊ ሂደት አለው። የከበርቴ ሥርዓት ከሞላ ጎደል አራት ነገሮችን ማሟላት አለበት፦ 1) የካፒታል የግል ንብረትነት፣ 2) የመምረጥ ነጻነትና የንግድ-ነክ አውታሮች (enterprise) መኖር፣ 3) ውድድር፣ 4) በገበያ ላይ መተማመን። የ4ተኛው ዋና አንቀሳቃሽ ኃይል 'የዋጋ ተመን' ነው፣ ይኸም ራሱ የቻለ ንኡስ-ሥርዓት ሆኖ አራቱን የካፒታሊዝም ክፍላተ-አካላትን ያንቀሳቅሳል። ይህ ሂደት ገበያው ራሱ የምያቀርበው እንጂ በመንግሥት ጣልቃ ገባነት የሚንቀሳቀስ አይሆንም። ለዚህም ነው በ2ኛ ደረጃ 'የመምረጥ ነጻነት' ያስቀመጥኩት። ብርሃኑ 'ነጻ መሆን' የሚለውም ከዚሁ ጋር የሚገጥም ይመስለኛል።

በገጽ 578 ደራሲው ብሶቶችንና የፖለቲካ ጉዳዮች በጠመንጃ መፍታት ለዴሞክራሲ ግንባታ ተመራጭ እንዳልሆነ ከተወያየ በኋላ "ብሶት እየጨመረ ሲሄድ (ግን) ባጭር

ግዜ እንኳን ባይሆን እያዳር ለመንግሥት የራስ ምታት መሆኑ አይቀርም" ይላል። ይህ ትክክለኛ አባባል ነው፣ እኔም ሙሉ በሙሉ የምሰማማበት ነው። አንድነን ሕዝብ በኃይል ረግጦ መግዛት አይቻልም፣ የኋላ ኋላ ሕዝቡ ማመጹ አይቀርም። 'በትረ ያፀንዕ ኃይለ መንግሥት' የሚለው የጥንት ፈሊጥ አሁን ካለንበት የመጠቀ የሳይንስና የተክኖሎጂ ባህል (አድማሰዊ መልኩ ማለቴ ነው) የሚጣጣም አይደለም። ዱላ ብቻ የምያዘወትር የፖለቲካ ሥርዓት ደግሞ ወይ ዱላው ከመደብደብ ብዛት እየተቆራረጠ ያልቃል ወይ ደግሞ አንድ ቀን በአእላፍ የሚቆጠሩ ዱላዎች (የሕዝብ መከታዎች) በአንድነት ይፈልጡትና ድራሹን ያጠፉታል። የሚመረጠው ታድያ የሰላሙ መንገድ ነው! በልዝብ ተደራድሮ ችግሮችን መፍታት እንዴት ያለ ግሩም ፀጋ ነው! በደምብ አሰላስለን ካሰብንበት ደግሞ ስንት ግዜስ ደማችን ይፍሰስ?

በገጽ 580-81 ደራሲው የምዕራብ አገሮች "ዓለምን በሚሰብኩት የዴሞክራሲ አስፈላጊነትና የሰብአዊ መብት መጠበቅ መርህ አኳያ ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋር ያላቸው ወዳጅነት ክፉኛ እያሳፈራቸው መሆኑን ይታወቃል" ካለ በኋላ አመሪካ ከጥቅምዋ አንጻር አይታ በኢትዮጵያ መረጋጋት እንጂ "የህአዴግን ኢዴሞክራስያዊ እርምጃ በመደገፍ እንዳልሆነ በግልጽ ታይቷል" በማለት ያክልበታል። በተጨማሪም "ይህም ቢሆን እንኳ በአመሪካ የተለያዩ የሥልጣን እርከኖች በአጭር ግዜ እንኳን የቱ ይበልጥብናል? ጊዝያዊ መረጋጋት ወይስ የዴሞክራስያዊ ሥርዓት ግንባታ ጥያቄ ብዙ እያከራከራቸው እንደሆነ በውጭ ጉዳይ መሥርያ ቤታቸውና በኮንግረስ አባላት መካከል ያለው ልዩነት ያሳያል" በማለት ይከራከራል።

ቀደም ብየ ከገጽ 562-63 በማያያዝ ያቀረብኩትን ትንተና ይህ ከላይ የተጠቀሰውን የብርሃኑ ሓተታ አሁንም ቢሆን እጅግ በጣም የተሳሳተ ነው። በአንጻሩ የምዕራብ አገሮች የትኛው ኃይል ነው ብሔራዊ ጥቅማችንን የምያስጠብቀውና የምያራምደው ነው የሚሉት እንጂ የዴሞክራሲ ግንባታ በኢትዮጵያ (በሌሎች ታዳጊ አገሮችም ጭምር) ጉዳያቸው አይደለም። በእርግጥ አልፎው አልፎው እነዚህ የምዕራብ አገሮች በተመጽዋች አገሮች ላይ ሰብአዊ መብትና ዴሞክራሲን አስመልክቶ ጫና ስያደርጉ አይተናል፣ ግን ከመርሕም ከፖሊሲም አንጻር ተቀዳሚ ተግባራቸው አይደለም።

ብርሃኑ በገጽ 586 "የሕዝብ ፖለቲካ በግል ቂምና ጥላቻ አይወሰንም" ያለውን በመርህ ደረጃ ሙሉ በሙሉ የምስማማበት ነው። ይህ አባባል ትክክለኛ ብቻ ሳይሆን እጅግ በጣም አሳሳቢና ለወደፊቱ በኢትዮጵያ የዴሞክራሲ ሂደት ላይ ትልቅ ሚና የሚጫወት ለመሆኑ ማንኛውም የፖለቲካ ድርጅት አበጥሮ ማወቅ ያለበት ጉዳይ ነው። ለዚሁ መሰረታዊ መፍትሔ ልናገኝለት የምንችል የአስተሳሰብ ለውጥ ስናመጣ ብቻ ነው። ይኸንንም አስመልክቶ ደራሲው በገጽ 589 በትክክል አሰቀምጦታል።

በገጽ 590ና 591 ደራሲው "አንድ ድርጅት የኢህአዴግን ተቃዋሚ ስለሆነ ብቻ በቀጥታ ይኸንን ያሟላል ሊባል አይቻልም" ያለውን ሚዛናዊ ትንተና ነው። በእርግጥም በርቱዕነት ካየነው ጸረ ኢህአዴግ ማለት ዴሞክራቲክ ማለት አይደለም።

በገጽ 592 ብርሃኑ በጣም የምያስደስት አስተሳሰብ ይዞ ስለቀረበ ሙሉ በሙሉ እንዳለ ላሰቅምጠው፦ "ከሁሉም በላይ ግን በዚህ መልክ የሚመጣ ሽግግር

የኢትዮጵያውያንና የሕዝቧን በአንድነት መቆም በማሳየት ለአገራችን ክፉ የሚመኙ ኃይሎችን ማሳፈር ብቻ ሳይሆን ከመተናኮስ እንዲቆጠቡ ያደርጋል። የተከፋፈለ ቤት ለዝርፍያ እንዲመች ሁሉ ውስጡ ጤነኛ ያልሆነ አገር ለውጭ ጠላቶች እንደሚመች ከእኛ በላይ ከታሪክ የሚማር ያለ አይመስለኝም፡" ግሩም አባባል! ይህ በተለይ ከኔ አመለካከት ጋር የሚገጥምና ብዙ ግዜ በተለያዩ ጽሑፎቼ ከሳመርኩባቸው አንዱ ርእሰ-ነገር ነው።

በገጽ 595 በሰላማዊ ሰልፈኞችና በመንግሥት ኃይሎች በተደረገው ግጭት ደራሲው "መንግሥት ሆን ብሎ ግጭቱን መተንኮሱ" እንደምያምንበት ከገለጸ በኋላ "ነገር ግን ሽክሙን መንግሥት ላይ በመጣል ልናልፈው አንችልም" በማለት ሚዛናዊ ሓተታ ለማቅረብ ሞክሯል። ከዚሁ ርእሰ-ነገር ሳይወጣ ደግሞ፡ የትግል ስልቱን እንዴት እንደሚለይ ለማስረዳት በገጽ 596 "ስለዚህም ግጭት ሲተነኮስ ወድያውኑ ለዝያ አፀፋ ለመስጠት አይቸኮልም" ይላል ብርሃኑ። የሰላም መንገድ፡ የግጭት አፈታት ስልቶች በውይይት ብቻ ማቅረቡ ግን በቂ ላይሆን ይችላል። መጀመርያ የዚሁ የሰላም ቅድመ-ሁኔታ፡ የመቻቻል ባህል ማዳበር፡ አስፈላጊ ነው። ይኽንንም መተግበር የምንችለው ትምህርታዊ ተቋሞችና የብዙሓን ማገናኛዎች የጠፈ ቅስቀሳ ስያካሂዱና ብሎም (ከፍ ብለን እንዳየነው) የምልአተ ሕዝቡ አስተሳሰብ ሲቀየር ነው።

የሕዝቡን አስተሳሰብ ለመቀየር እንግዴህ ሰፊና ጠለቅ ያለ ትምህርት ማካሄድ ሊኖርብን ነው። ይኽንንም በተመለከተ፡ ብርሃኑ በገጽ 606 አስፍሮታል። የሰላሙ መንገድም የሚመረጠው፡ 1) ብርሃኑ እንዳስቀመጠው የትጥቅ ትግል ብዙ መስዋእትና ዋጋ ይከፈለዋል፣ 2) አሁን እንደ አማራጭ የትጥቅ ትግልን ያሰበ ወይም የተገበረ ቡድን ወይም ፓርቲ በቀላሉ 'አሸባሪ' የሚል መጥፎ ስም ይለጠፍበታል።

በገጽ 610 አገርን በማስቀደም ደራሲው "የአገራዊ ብሔረተኝነትን ማጎልበት" "ትልቅ የኢኮኖሚ ፋይዳ" እንዳለው ይገልጻል፣ ይኽም ከኔ እምነትና አስተሳሰብ ጋር የሚገጥም ነው፡ እንዲህ ያለ ያገር ስሜት ከሁሉ በፊት መምጣት አለበት። ማንኛውም የብሔርና የብሔረሰብ አባል ቋንቋውንና ባህሉን ለማዳበርና የራስ ገዝን መስተዳድር መብቱ እንዲከበርለት አስፈላጊ ሲሆን፡ ይህ ሰፊ መብት ግን የኢትዮጵያን አንድነት የምያጠናክር እንጂ የምያናጋ መሆን የለበትም። ኢትዮጵያዊ መንነት መቅደም ይኖርበታል። ይኽንን በተመለከተ በርካታ ጽሑፎች አቅርብያለሁ። በቅርቡ በሃርቫርድ ዩኒቨርሲቲ በኢትዮጵያ ተማሪዎች ማሕበር አስተናጋጅነት (November 12, 2006) Ethnicity and National Identity in Ethiopia የሚለውን ርእሰ-ነገር ይዞ የቀረበውን ትምህርታዊ ጉባኤ ላይ አንዱ ተናጋሪ ነበርኩኝ። የጽሑፌ ዋና መልእክት የብሔሮች መብት ከኢትዮጵያ አንድነት ነጥለን ማየት እንደሌለብን ነበር።

በመጨረሻም፡ እኔ ብዙ ግዜ በጽሑፎቼ ላማሳሰብ እንደመኮርኩት፡ ብርሃኑም በገጽ 611 እንደጠቀሰው ኢትዮጵያ አገራችን "የሁሉንም ዜጎች ጉልበትና አእምሮ ትፈልጋለች።" ከዚህ ቀደም ርሃብን አስመልክቶ ግዙፍና ታሪካዊ ግብረ-ኃይል ስለሚጠይቅ ሓለፊነቱ በመንግሥት ባለሥልጣናት ብቻ መተው እንደማንችል፣

በውጭ የምንገኝ ምሁራንና ሞያተኞች ድርሻችንን መከፈል እንዳለብን ሐሳብ አቅርቤ ነበር። የዛሬ ስድስት ወር ገደማ በአንድ የሓሳብ ልውውጥ መድረክ ላይ ፕሮፌሰር ዶናልድ ለቪን የኔን ሐሳብ በመደገፍ አቋማቸውን ግልጽ አድርገዋል። መድረኩ የተካሄደውና የተቀናበረው በ Ethiopian Institute for Non-Violence and Peace Studies (view topic – Getz # 6) ሆኖ የወብሳይቱ አድራሻ www.eineps.org ነው። አሁን የምያስፈልጉን ሁለት ነገሮች ናቸው፡ 1) በሰላም ችግሮቻችን መፍታት፣ 2) ኢትዮጵያ የሁላችን 'ጉልበትና አእምሮ' ስለምትፈልግ ይኽችን ታሪካዊት አገር በአንድነት እንገንባት። ሰለሆነም የሰላሙና የእርቅ ጉዳይ ይጀመርና መንግሥት ምሕረትን በማወጅ የፖለቲካ እስረኞችን ይፍታ፣ በቅርብም በሩቅም ያለነው ኢትዮጵያውያን ደግሞ ለአገራችን ድርሻችንን እናበርክት።

All Rights Reserved © Institute of Development and Education for Africa (IDEA), Inc. 2007